# ጥናት አንድ ሆሴዕ 1፡1-2፡1 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ትንቢቱን የተናገረው ሰው ሆሴዕ እንደሆነና አባቱም ብኤሪ እንደሚባል ተጽፎልናል፤ በተጨማሪ የምናየው ነገር ደግሞ፤ ነብዩ ሆሴዕ ስላገለገለበት ጊዜ ሲሆን ይህም፤ ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ በተባሉ አራት የይሁዳ ነገሥታት ዘመን፤ በእስራኤል በኩል ደግሞ በንጉሥ ዮአስ ልጅ በኢዮርብአም ዘመን እንደተናገረ እናያለን። ምንም እንኳን የትንቢቱን መልዕክት ያመጣውና የተናገረው ነብዩ ሆሴዕ ይሁን እንጂ፤ የመልዕክቱ ባለቤት የሆነው እግዚአብሄር በመሆኑ "የእግዚአብሄር ቃል" በማለት ነው የሚያቀርበው።
2. ሆሴዕ የትንቢቱን መልዕክክ ከእግዚአብሄር በተቀበለበት ወቅት፤ በእግዚአብሄር ዓይን ሲታይ ምድሪቱ ከእግዚአብሄር መራቅ ብቻ ሳይሆን ምንዝርና እያደረገች እንደሆነ ነው የተገለጸው። የዚህን ሰው ተልዕኮ ልዩ የሚያደርገው፤ እግዚአብሄር ሊያዘው የማይችል የሚመስል ትዕዛዝ የተቀበለ ነብይ መሆኑ ነው። እኔ መቼም ሆሴዕ እግዚአብሄር ጋለሞታ ሴት እንዲያገባና ልጆች እንዲወልድ ሲነግረው ለጊዜው በድንጋጤ የሚዋጥ ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ይህ አድራጎት በእግዚአብሄር በራሱ ዘንድ አጸያፊ ሆኖ ስለሚታይ ነው።
3. ነብዩ ከእግዚአብሄር የተቀበለውን መመሪያና ትዕዛዝ ተቀብሎ በመሄድ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ቢኖር፤ የዴቤላይምን ሴት ልጅ ማለትም የተባለችውን ሴት እንዳገባና ከእርሷም ወንድ ልጅን እንደወለደ እንመለከታለን። እግዚአብሄር በመጀመሪያ በቁ2 ላይ ለነብዩ በሰጠው ትዕዛዝና በቁ4 ላይ ለሁለተኛ ጊዜ በሰጠው መመሪያ መካከል ቢያንስ ቢያንስ የዘጠኝ ወር ልዩነት ማለትም ልጅ ተጸንሶ የሚወለድበትን ያህል ጊዜ መኖሩ ግዴታ ሲሆን፤ ጊዜው ግን ከዘጠኝም ወር ሊበልጥ ይችላል።
4. ከሆሴዕና ከጎሜር የተወለደው ወንድ ልጅ ስሙ ኢይዝራኤል ተብሎ እንደተጠራ እናነባለን፤ ይህንንም ስም ለነሆሴ ልጅ ያወጣለት አባቱንና እናቱን ሳያማክር እግዚአብሄር ራሱ ነበረ። "በዚህ ቀን" የሚለው አባባል የሚጠቁመን በቁ4 ላይ እግዚአብሄር በኢዩ ቤት ላይ ስለሚያመጣው ቅጣትና፤ የእስራኤል መንግሥት ደግሞ እንዲያከትም ሊያደርግ እንዳለው የተናገረበትን ወቅት ነው የሚጠቁመው።
5. በዚህ በቁ6-7 ላይ የሆሴዕን ሁለተኛ ልጁን እግዚአብሄር ሎሩሃማ በማለት ስምን ሲያወጣላት፤ እስራኤል እግዚአብሄርን መከተልና መፈለግ ትቶ ወደ ሌሎች አማልክት ፊቱን የመለሰበት ጊዜ በመሆኑና የእግዚአብሄር ልብ ስላዘነ፤ ከእንግዲህ ወዲህ እንደማይራራላቸውና ይቅር እንደማይላቸው ለማሳሰብ ያወጣው ስም እንደሆነ ቁጥሮቹ ይነግሩናል። እስራኤልና ይሁዳ በዚያን ወቅት የነበሩበትን ሁኔታ ስናነጻጽር ይሁዳ ገና እስራኤል የነበረችበት ሁኔታ ውስጥ እንዳልገባች፤ ይህንንም ያልኩበት ምክንያት በቁ7 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ራሱ ለይሁዳ እንደሚራራና ሊያድናትም እንደተዘጋጀ ሲናገር እንመለከተዋለን።
6. እነዚህ ቤተሰቦች ከወለዷቸው ልጆች መሃል መልካም የሆነ ዜናን ይዞ የመጣ አንድም ልጅ አናይም፤ ሶስቱም እያንዳንዳቸው በተለይም ለእስራኤል አሳዛኝና አስደንጋጭ የሆነ ዜና ይዘው ነው የመጡት። እግዚአብሄር በብዙ ሥፍራ ሕዝቡን እንደማይጥልና እንደማይተው ከተናገረባቸው ክፍሎች መሃል መዝ 94፡14 ሲሆን፤ መዝሙረኛው "እግዚአብሄር ሕዝቡን አይጥልምና፤ ርስቱንም አይተውምና" ይላል። ስለዚህ ጌታ የተስፋ ቃሉን የሚያጥፍ ስላልሆነ ሌላ ትርጉም እንደሚኖረው ይመስለኛል። በዚህ ስፍራ ላይ እየተናገረ ያለው የሚመስለኝ፤ እናንተ በተግባራችሁና በኑሯችሁ እንደ አምላካችሁ አልቆጠራችሁኝም ስለዚህም እኔም ደግሞ ሕዝቤ ሆናችሁ እንድትቆጠሩ አልፈልግም ወይም አልፈቅድም እንደሚል ነው የሚገባኝ።
7. የእስራኤል ልጆች በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምንም ተስፋ የሌላቸውና በአምላካቸውም ፊት በሃጥያታቸው ምክንያት የሚመጣባቸውን ቁጣ ለመቀበል ጊዜው ቅርብ እንደሆነ በምዕራፉ ሁሉ የተመለከትን ሲሆን፤ በቁ 10-11 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ግን የምንመለከተው ነገር ቢኖር፤ እግዚአብሄር አምላካቸው ለልጆቹ የሚያይላቸው ነገር ብሩህ ጊዜ እንደሚመጣላቸው እና ለምድራቸው ታላቅ ነገር እንደሚጠብቃት መልካም ዜናን ነው የሚመለከትላቸው።

# ጥናት ሁለት ሆሴዕ 2፡2-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ልጆችዋ ለእናታቸው እንዲነግሩ የታዘዙት ነገር ቢኖር፤ እርሷ የእግዚአብሄር ሚስት እንዳልሆነች፣ እርሱም ደግሞ የእርሷ ባል እንዳልሆነ፤ ከፊትዋ የዘማዊትነት አስተያየትን፣ ከጡቶችዋም መካከል ምንዝርናዋን እንድታስወግድ ነው። በልጆችዋ የተነገራትን ባትሰማ ግን፤ ልብሷን ገፎ ርቃኗን በማስቀረት እንደተወለደችበት ቀን እንደሚያደርጋት፤ እንደ ምድረበዳ፣ እንደደረቅም ምድር እንደሚያደርጋት፤ በውሃ ጥም እንደሚገድላት፣ የምንዝርና ልጆች በመሆናቸው ለልጆችዋም እንደማይራራ ይነግራታል።
2. ይህች አመንዝራ ሴት ከውሽሞችዋ ልታገኝ የምትጠብቃቸው ነገሮች፤ እንጀራ፣ ውሃ፣ ሱፍና የሃር ልብስ፣ ዘይት፣ እንዲሁም መጠጥ ናቸው። በእግዚአብሄር ዘንድ ሁሉ ነገር ሙሉ እንደሆነና ለእስራኤል አንዳች በሌለበት በምድረበዳ እንኳን የሚበሉትንና የሚጠጡትን የሰጠ አምላክ እንደሆነ እንደተለማመደች ይታወቃል፤ እኔ የሚመስለኝ ግን አበሻ በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል እንደሚለው፤ ሁልጊዜ በውጭ ያለው እንደሚሻል ስለሚመስል ይህችም ሴት የተሻለ የመሰለውን ለመቅመስና ለመለማመድ ካላት ጥማት፤ በልቧ ለባሏ ከመሰጠት ይልቅ ልቧ ወደውጭ ስለሚል ይመስለኛል።
3. እግዚአብሄር ይህንን በማድረግ ሊያመጣ የፈለገው ውጤት በቁ7 ላይ የምናነበው “ከዚያም እንዲህ ትላለች፤ ወደ ቀድሞ ባሌ እመለሳለሁ፤ የፊተኛው ኑሮዬ ከአሁኑ ይሻለኛልና።” ሃሳብ ከነበረችበት አስከፊ ህይወት ውስጥ ወጥታ ተመልሳ የእርሱ ለመሆን እንድትወስን ለማድረግ ነው። እስራኤል የነበራት ሌላው ችግር፤ በእጇ የነበረው ነገር ሁሉ ማለትም፤ እህሉ፣ ዘይቱ፣ የወይን ጠጁ፣ ብሩና ወርቁ ሁሉ ከእግዚአብሄር ዘንድ የተገኘ እንደሆነ አድርጋ ማየት የተሳናት ጊዜ ነበረ።
4. እህሉንና የወይን ጠጁን በደረሰ ጊዜ እንደሚወስድባት፣ እርቃኗን እንዳትሸፍንበት ሱፍና የሃር ልብሱን መልሶ እንደሚወስድባትና ይህንንም በማድረግ በውሽሞችዋ ፊት ሁሉ ነውሯን እንደሚገልጥ፣ የደስታ በዓሎችዋን፣ የዓመት በዓሎችዋን፣ የወር መባቻዎችዋን፣ ሰንበቶችዋንና የተመረጡ በዓሎቿን ሁሉ ያስወግዳል። እግዚአብሄር ፍቅረኛውን ከሌሎች ጋራ ለማየት አለመፈለጉና እርሷንም በተቻለው ወደ እርሱ ለመመለስ ይህንን ሁሉ ለማድረግ መነሳቱ የሚያስታውሰኝ ባህርይ ቢኖር እግዚአብሄር ቀናተኛ አምላክ ነው የሚለውን ባህርዩን ነው።
5. ይህች እንደ እግዚአብሄር ሚስት በመሆን የተጠራችው እስራኤል የበዓልን አማልክትን በማምለኳና በማጠኗ ምክንያት ከእግዚአብሄር ስለሚያገኛት ነገር ቁጥር 13 የሚነግረን እንደምትቀጣ ነው። የእግዚአብሄር ቃል በተለያየ ሥፍራ እግዚአብሄር የሚወደውን ሁሉ እንደሚቀጣ የሚናገር ሲሆን፤ በተለይም በዕብ 12፡6-11ድን ስናነብ፤ እግዚአብሄር የማይቀጣው ልጅ ካለ እርሱ ልጅ ሳይሆን ዲቃላ እንደሆነ ሲናገር፤ በተጨማሪም ደግሞ ቅጣቱ ከቅድስናው እንድንካፈል እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ይነግረናል።
6. እግዚአብሄር እስራኤልን ከቀጣ በኋላ መልካም ፍሬ የሚፈራበት ጊዜ እንደሆነ፤ እነዚህ መልካም ፍሬዎችም ከእስራኤል የመነጩ ሳይሆኑ ራሱ እግዚአብሄር የሚሰራቸው ነገሮች ስለሆኑ በዚያ የምናያቸው ቃላሮች ሁሉ ትኩረታቸውን ያደረጉት በእግዚአብሄር ላይ ነው። እግዚአብሄር እነዚህን ነገሮች በእስራኤል ህይወት ውስጥ በሚፈጽምበት ጊዜ፤ “በዚያን ጊዜ ከግብጽ እንደወጣችበት ቀን፤ እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች።” በማለት እስራኤል በዚያን ሰዓት የሚሰማትን የደስታ ስሜት በዝማሬ እንደምትገልጸው ይነግረናል።
7. የእግዚአብሄርንና የእስራኤልንና ግንኙነት ለመናገር ጸሐፊው በተለያየ መንገድ ለመግለጽ የተጠቀመበት አንድ ሃሳብ “የባልና የሚስት” ግንኙነት እንደሆነ በቁ16 ላይ “ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ” የሚለውና፤ በቁ19-20 ላይ ብቻ ሶስት ጊዜ “አጭሻለሁ” እያለ የሚናገረው የዚህን ዓይነት ግንኙነት በመሃላቸው እንዳለ በግልጽ ይጠቁመናል። ቅደም ተከተሉ፤ እግዚአብሄር ለሰማያት ትዕዛዝ መስጠት ወይም መመለስ፤ ቀጥሎ ሰማይ ለምድር ምላሽ መስጠት፣ ከዚያ ቀጥሎ ምድር ደግሞ ለተዘራባት ነገር መልስ መስጠት ነው።
8. “እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች” የሚለውን ሃሳብ እኔ የምረዳው፤ ጌታን በተቀበልንባቸው በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ዝማሬን ለጌታ ስንዘምር የትኛው ሰው ያየኛል፣ ከጎኔ ያለው ሰው ምን ይለኛል ወይም ደግሞ ድምጼን የሚሰሙ ሰዎች ጥሩ ድምጽ እንደሌለኝ ያስባሉና፣ የመሳሰሉትን ዛሬ በአዕምሯችን የምናመላልሳቸው ሃሳቦች በዚያን ጊዜ ምንም ዓይነት ቦታ አንሰጣቸውም ነበረ፤ ስለዚህ አሁንም እግዚአብሄር ለሚያደርግልን ነገር ምላሻችን እንደ ልጅነት ጊዜያችን ተለቀንና ተፈትተን መዘመር ያስፈልገናል።

# ጥናት ሶስት ሆሴዕ 3፡1-4፡19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ በቁ1 ላይ ነብዩ ሆሴዕ ከእግዚአብሄር ሲቀበል የምንመለከተው ትዕዛዝ፤ ሚስቱ ጎሜር እንደለመደችው ከባሏ ወጥታ ከሌሎች ወዳጆችዋ ጋራ በመማገጥ ላይ ስለነበረች ሆሴዕ መልሶ ወደ ቤቱ እንዲያስገባትና እንዲወዳት ነው የታዘዘው። እግዚአብሄር ሆሴዕን ይህንን ትዕዛዝ ያዘዘበት ዋነኛው ምክንያት በዚሁ በቁ1 ላይ እንደሚነግረን፤ እስራኤል እግዚአብሄርን ማምለክ ትታ ወደ ተለያዩ አማልክት በመሮጥ ላይ ስላለች፤ እግዚአብሄር በዚያን ወቅትም እንኳን ሕዝቡን እስራኤልን እንደሚያፈቅር በተጨባጭ ማስረጃ ለማሳየት ሲል ነው ነብዩ ይህንን እንዲያደርግ ያዘዘው።
2. ሆሴዕ ሚስቱ ለነበረችው ለጎሜር መክፈል ያስፈለገው ምክንያት፤ ምናልባት ይህች ሴት ከእነዚህ አብራ ከምታመነዝራቸው ሰዎች ላይ የነበረባት መክፈል የነበረበት እዳ ሊሆን እንደሚችልና ያንን ካልከፈለ ሊያገኛት እንደማይችል ሊሆን ይችላል ብዬ ነው የማስበው። እስራኤል የሚያልፍባቸው እነዚህ ሁለቱ የህይወት ደረጃዎች፤ በመጀመሪያ ለብዙ ዘመን ያለ አለቃና ያለ ንጉስ፣ ያለ መስዋዕትና ያለ ዓምደ ጣዖት፣ ያለ ኤፉድና ያለ ጣዖት ምስል መኖር ሲሆን፤ ይህ ሁሉ ካለፈ በኋላ ደግሞ እስራኤል አምላካቸውን እግዚአብሄርንና ንጉሳቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፣ በመጨረሻውም ዘመን በመንቀጥቀጥ ወደ እግዚአብሄርና ወደ በረከቱ መምጣት ናቸው።
3. በእነዚህ አስከፊ ድርጊቶች ምክንያት እንደ ተጎዱ ቁ3 የሚናገራቸው፤ የምድሪቱን ማልቀስ ስለሚነግረን የመጀመሪያዋ ጉዳተኛ ምድሪቱ ናት፤ ሁለተኛው ተጎጂ ደግሞ በምድሪቱ ላይ የሚኖሩት እንደ ኮሰመኑ ሲናገር፤ ሶስተኛ ደግሞ የምድር አራዊት፣ የሰማይ ወፎችና፣ የባህር አሶች እንዳለቁ ነው የምናየው። አገሪቱ ለገባችበት አስከፊ ሁኔታ ቁ4-5 ተጠያቂ የሚያደርጋቸው፤ በአንደኛ ደረጃ ካህናቱ ሲሆኑ፣ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ሕዝቡ፣ ሶስተኛም ነብያቱ እንደሆኑ ነው የሚነግረን።
4. የታማኝነት፣ የፍቅርና፣ እግዚአብሄርን ማወቅ አለመኖር በቁ3 ላይ ለእስራኤል ችግሮች እንደሆኑ ብናይም እንኳን፤ በቁ 6 ላይ ስንመለከት ግን ለዚህ ሁኔታ ሁሉ የዳረጋቸው ምንጩ የህዝቡ እውቀት ማጣት ወይም በቁ3 ላይ እግዚአብሄርን ያለማወቅ የተባለው ችግር ነው። በዚሁ ቁጥር ላይ እንደምናየው ካህናቱ ለራሳቸው እግዚአብሄርን ለማወቅ መሞከርና የእግዚአብሄርን ሕግ ለማጥናት ካለመትጋታቸው ሌላ፤ ለህዝቡ እግዚአብሄርን ማወቅ እንዲችልና ቃሉን መጠበቅ እንዲችል ማስተማርን ችላ ስላሉ ሃላፊነቱን በእነርሱ ላይ እንደወደቀ እናነባለን።
5. እግዚአብሄር የካህናት መብዛት የህዝቡን ሃጥያት እንዳበዛው መናገሩ፤ ሁልጊዜ ብዙ ካህናት ባሉ ቁጥር የህዝብ ሃጥያትም እንደዚያው እየበዛ ይሄዳል ማለት ሳይሆን፣ እግዚአብሄርን የማይፈሩና፣ እግዚአብሄርን ማወቅ ለህዝብ ያማያስተምሩ ካህናት በበዙ ቁጥር የህዝብ ሃጥያትም ይጨምራል ማለት እንጂ፤ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያላቸው ካህናት መኖራቸው ለህዝብ በረከት ነው። ይህ ማለት ህዝቡ ሃጥያት በሰራ ቁጥር መስዋዕት ማቅረብ ስላለበት ከዚያም ለካህናቱ የሚሆን ምግብ ስለሚተርፍላቸውና፤ ህዝቡ ደግሞ ብዙ መስዋዕት ባቀረበ መጠን ብዙ ስለሚያገኙ፤ ህዝቡ ብዙ ሃጥያት መስራቱን እየተስማማቸው መጥቷል ማለት ነው።
6. እግዚአብሄርን ትተዋል፣ ራሳቸውን ለአመንዝራነት ሰጥተዋል፣ ራሳቸውን ለወይን ጠጅ አሳልፈው ሰጥተዋል፣ ከጣዖት ምክር ይጠይቃሉ፣ ከበትራቸው ለጥያቂያቸው መልስ ይጠብቃሉ፣ ለአምላካቸው ታማኝ አልሆኑም፣ በተራሮች ጫፍ ላይ ይሰዋሉ፣ በኮረብታዎች ላይም የሚቃጠል ቁርባን ያቀርባሉ። ሴቶች ልጆቻቸውን ዘማዊያን፣ ምራቶቻቸው ደግሞ አመንዝሮች እንዲሆኑ ይፈቅዳል፣ ሴቶች ልጆቻቸው ዘማውያን፣ ምራቶቻቸው አመንዝሮች ሲሆኑ እግዚአብሄር አይቀጣቸውም፤ ወንዶቻቸው ከጋለሞቶች ጋራ ይሴስናሉ፣ ከቤተ ጣዖት ዘማውያን ጋራም ይሰዋሉ።
7. ይሁዳ ከእስራኤል ጋራ እንዳይተባበር ወይም እነርሱን እንዳይመስል የተነገረው፤ እንደ እስራኤል እንዳያመነዝር፣ ወደ ጌልጌላ እንዳይሄድ፣ ወደ ቤት አዌን እንዳይወጣ፣ ሕያው እግዚአብሄርን ብለው እንዳይምሉ ነው። ይሁዳ የእስራኤልን ፈለግ መከተል የሌለበት፤ እስራኤል እንደ እልከኛ ጊደር ስለሆነ፣ ኤፍሬም ወይም እስራኤል ከጣዖት ጋራ ስለተጣመረ፣ ስካራቸው ሲያበቃ እንኳን ዘማዊነትን ስለማያቆሙ፣ ገዢዎቻቸው ነውረኛን ነገር አጥብቀው ስለሚወዱ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶችን ሰዎች እግዚአብሄር በመልካም መስክ ውስጥ እንደማያሰማራቸው ቁ16 ግልጽ አድርጎታል።
8. እግዚአብሄር ከእስራኤል ምድር ጠፍተዋል ወይም በአገሪቱ ውስጥ እንደሌሉ አድርጎ እስራኤልን የሚከስባቸው ሶስቱ ነገሮች፡ የመጀመሪያው ታማኝነት እንደሌለ፣ ሁለተኛው ደግሞ ፍቅር የሚባል ነገር እንደሌለና፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሄርን ማወቅ የሚባል ነገር በምድሪቱ ላይ እንደሌለ ነው የሚከሰው። በምድሪቱ የሞላው ነገር፡ ርግማን፣ መዋሸት፣ መግደል፣ መስረቅ፣ ማመንዝር የበዛ ሲሆን፤ ከእነዚህም በተጨማሪ ቃል ኪዳንን ማፍረስና ግድያ ምድሪቱን እንዳጥለቀለቃት ነው እግዚአብሄር የሚከሰው።

# ጥናት አራት ሆሴዕ 5፡1-6፡11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ3 ላይ ኤፍሬምን አስመልክቶ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን፤ ከእነዚህም የመጀመሪያው እግዚአብሄር ስለ ኤፍሬም ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ የሚናገረው ሲሆን፤ ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ ኤፍሬም እንዳመነዘረ የተናገረው ነገር ነው። በዚሁ ቁጥር ላይ እስራኤልን አስመልክቶ ደግሞ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች፤ አንደኛው ልክ እንደ ኤፍሬም እስራኤልም ከእግዚአብሄር የተሰወረች እንዳልሆነች ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እስራኤል እንደረከሰች የሚናገር ነው። እግዚአብሄር ኤፍሬምንና እስራኤልን በምንዝርናና በእርኩሰት እንደሚመላለሱ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፤ የእኔንም የእለት እለት ኑሮ ከእርሱ የተሰወረ እንዳልሆነ ያስገነዝበኛል።
2. ኤፍሬም፣ እስራኤልና ይሁዳ በሃጥያታቸው ከተሰናከሉ በኋላ በቁ6 ላይ ሊያደርጉ ሲሞክሩ የሚታዩት እግዚአብሄርን ፍለጋ የበግና የፍየል እንዲሁም የቀንድ ከብቶቻቸውን ነድተው መስዋዕት ለመሰዋት ሲሄዱ ነው የምናያቸው። ኢሳ 55፡6 “እግዚአብሄር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፣ ቀርቦም ሳለ ጥሩት” በማለት እንደሚናገረው፤ እነዚህን ሰዎች እግዚአብሄር በጣም በቅርብ ሆኖ በነብያቱ በተለያየ መንገድ በሚናገራቸውና ሊመልሳቸው ሲሞክር እንቢ ስላሉትና ስላልመለሱለት፤ አሁን ደግሞ እግዚአብሄር በተራው ጀሮውን ሲነፍጋቸው ነው የሚታየው።
3. ቁ12 ላይ ስንመለከት ለኤፍሬም እንደ ብል እንደሆነለት፣ ለይሁዳ ህዝብ ደግሞ እንደ ነቀዝ እንደሆነላቸው ሲናገር፤ ወረድ ብሎ በቁ14 ላይ ደግሞ ለኤፍሬም እንደ አንበሳ እንደሚሆንለት፣ ለይሁዳ ደግሞ እንደ ደቦል አንበሳ እንደሚሆንለት አድርጎ ይናገራል። ለነዚህ ሁለት ነገዶች አንበሳና የአንበሳ ደቦል እሆንባቸዋለሁ ሲል፤ እሰባብራቸዋለሁ፣ አደቃቸዋለሁ፣ ነጥቄ እወስዳቸዋለሁ፣ ከእጄ ሊያድናቸው የሚችልም ማንም የለም ማለቱ ነው። ይህን ሁሉ በኤፍሬምና በይሁዳ ላይ ለማድረግ የወሰነው በደላቸውን አውቀው ወደ እርሱ እስኪመለሱ ድረስ ነው።
4. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ነብዩ ሆሴዕ ህዝቡን በፍቅር የሚጠይቃቸው፤ ሁሉም በአንድነት እንዲመጡና ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ ሲሆን፤ ይህንን ደግሞ ከልባቸው ካደረጉት የሰበራቸው አምላክ እንደሚጠግናቸው፣ ያቆሰላቸው አምላክም ደግሞ እንደሚፈውሳቸው ይነግራቸዋል። ይህ ነብዩ ያመጣው ሃሳብ ኤፍሬምና ይሁዳ ከሄዱበት መንገድ ሙሉ በሙሉ የተለየና ምንም የማይገናኝ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ ፊታቸውን የመለሱት ወደ ታላቁ የአሶር ንጉስ ሲሆን፤ ሆሴዕ ግን የሚመክራቸው ሁኔታውን ወዳመጣባቸው ወደራሱ ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ ነው። የአንድ ቀን ነገር ሳይሆን ዘወትር እግዚአብሄርን ለማወቅ በተጉ ቁጥር እግዚአብሄር ራሱን መግለጡ ልክ የፀሐይን መውጣት ያህል እርግጠኛነት ነበረው።
5. በቁ4 ላይ እግዚአብሄር በህዝቡ ሁኔታ እያሳዘነው ያለውና የሚናገረው አንድ ነገር ቢኖር፤ ኤፍሬምም ሆነ ይሁዳ ለእርሱ ፍቅርን የሚሰጡበት ቀናቶች ሲኖሯቸው፤ ፍቅራቸው ግን ልክ እንደ ማለዳ ጉም ወይም ደግሞ ወዲያው ታይቶ እንደሚጠፋ እንደሚጠፋ የጠዋት ጤዛ ሆኖበት ነው ሃዘኑን የሚገልጸው። እነዚህ እግዚአብሄር የህዝቡን ፍቅር በቋሚነት ለማግኘት የወሰዳቸው ነገሮች፤ በነብያቶቹ አፍ መቆራረጥ እና ፍርዱን እንደ መብረቅ በላያቸው ማብራት ነበረ።
6. በዚህ በቁ6 ላይ እግዚአብሄር ሕዝቡ እንዲገባውና እንዲረዳው የፈለገው አንዱ መሰረታዊ እውነት፤ ከሚቀርብለት መሥዋዕት ይልቅ ምህረትን እንደሚሻ፤ ከሚቃጠለው መስዋዕት ይልቅ ደግሞ እርሱን እግዚአብሄርን ማወቅ እንደሚመርጥ እንዲገነዘቡ ነው የፈለገው። እግዚአብሄር ይህንን ሲል መስዋዕት ወይም የሚቃጠል መስዋዕት አታምጡልኝ አልፈልግም ማለቱ አይደለም፤ ነገር ግን በእርሱ ዓይን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ከመስዋዕት ይልቅ ምህረት መሆኑንና፣ ከሚቃጠል መስዋዕትም ይልቅ እግዚአብሄርን ማወቅ ቅድሚያ እንደሚሰጠው እንዲገባቸው ነው።
7. ኤፍሬም እግዚአብሄር ያመጣበትን ቁስል ባየ ጊዜ ፈውስ ፍለጋ የሄደው ቁ13 እንደሚነግረን እርዳታን ለመጠየቅ ወደ ታላቁ የአሶር ንጉስ መልዕክተኛ ነው የላከው፤ እግዚአብሄር ያቆሰለውን መፈወስ የሚችል፤ ወይም ደግሞ እግዚአብሄር የጣለውን ማንሳት የሚችል ማንም ስለሌለ የአሶር ንጉስ መፍትሄ ሊሆንለት እንዳልቻለና እንደማይችል እግዚአብሄር በዚሁ ቁጥር ውስጥ ይነግረናል።

# ጥናት አምስት ሆሴዕ 7፡1-8፡14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እስራኤል ሃጥያት ከመስራታቸው አልፎ እግዚአብሄር ደግሞ ያደረጉትን ሃጥያት እንደማያስታውስ ወይም እንደሚረሳ አድርገው እንደሚያስቡ፤ ሆኖም እግዚአብሄር በቁ2 ላይ ሃጥያታቸውን እንደማይረሳና ሁልጊዜ በፊቱ እንደሆነ ይናገራል። በእስራኤል ሕይወት በምናየው ሃጥያትን እንደሌለ አድርጎ ቆጥሮ እግዚአብሄርም እንደማያስታውሰው በሚቆጥረው ሰውና፤ ከልቡ ሃጥያተኛነቱን ተቀብሎ በእግዚአብሄር ፊት እውነተኛ የሆነ ንስሃ ለሚገባ ሰው እግዚአብሄር በገባው ቃል ኪዳን መሃል የሚታየው ልዩነት፤ ለእስራኤል ዓይነቱ ዘወትር ሃጥያቱን እንደሚያስብበትና ሁልጊዜ በፊቱ እንደሚያቆየው፤ በሃጥያቱ ለመጸጸተው ግን ሃጥያቱን እግዚአብሄር ተመልሶ እንደማያየው ነው የሚነግረን።
2. ቁ4 “እንደሚነድ ምድጃ ሁሉም አመንዝራ ናቸው”፣ ቁ6 “ልባቸው እንደ ምድጃ የጋለ ነው”፣ ቁ6 “ቁጣቸው…እንደሚነድ እሳት”፣ ቁ7 “ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው” በማለት በመደጋገምና ለሁሉም የጋራ የሆነው ቃል “ምድጃ” የሚለው ሃሳብ ነው። ጳውሎስ የሚናገረው መቀጣጠልና መንደድ የጌታን ሥራ ለመስራት ያለ የልብ ግለትን የሚናገር ሲሆን፤ የእስራኤል ልብ ግን እንደ ምድጃ የሚነደውና የሚቃጠለው በነጋታው ተነስቶ ተንኮልን ለማድረግ የሚገፋ አይነት ትኩሳት ነው።
3. በመጀመሪያ ደረጃ የኤፍሬምን ጉልበት እንግዶች እንደበዘበዙት፤ ሆኖም ግን እርሱ በጭራሽ እንዳላስተዋለ እናያለን፣ ሁለተኛ ደግሞ ኤፍሬም ጸጉሩ ሽበት እንዳወጣና እያረጀ እንደሆነ እርሱ አላስተዋለም፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የእስራኤል ትዕቢት በራሱ ላይ እንደመሰከረበት፤ ሆኖም ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሄር አልተመለሰም ወይም እርሱን አልፈለገም። ያልተገላበጠ ቂጣ ላዩ ሌላ ታቹ ሌላ መልክ ማለትም ሁለት ዓይነት መልክ እንደሚያመጣ ሁሉ፤ ኤፍሬምም ከአህዛብ ጋራ ሲደባለቅ፤ በአንድ ጎኑ የእግዚአብሄርን ህዝብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የአህዛብን መልክ ሁለት ዓይነት መልክ ይዞ እንደሚመላለስ ይጠቁመናል እላለሁ።
4. ኤፍሬም አዕምሮ እንደሌለው ሆኖ የማይባቸው፤ በቁ11 የሚታየው እግዚአብሄር እያለ ወደ ግብጽና ወደ አሶር ዘወር ማለቱ፣ ቁ13 እግዚአብሄር ሊታደጋቸው እየሞከረ በእርሱ ላይ ሃሰት መናገራቸው፣ ከልባቸው ወደ እግዚአብሄር አለመጮሃቸው፣ እሱ ያሰለጠናቸውን ያጠነከራቸው ሲሆን በእርሱ ላይ ማደማቸው። ዒላማውን እንደሳተ ቀስት ሲል ለእኔ የሚገባኝ፤ እግዚአብሄር ሊያደርሰውና ሊወስደው ያቀደበት ሥፍራ ሲኖር፤ ኤፍሬም ግን ሁልጊዜ የሚሄደውና የሚገኘው እንዲሄድ ባልታቀደለት ቦታ መሆኑን የሚናገር ነው።
5. የእግዚአብሄር ህዝቦች አደረጉ እያለ በቁ1 ላይ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በህጌ ላይ ዓምጸዋል ነው የሚለው። በእነዚህ በቁ2 እና በቁ3 ላይ በተነገሩት አነጋገሮች መሃል የሚታየኝ ቅራኔ ቢኖር፤ እግዚአብሄርን የሚያውቅ ሰው በጎ ነገርን የሚወድ፣ በጎን ለማድረግ ልቡ የሚቀና ሰው መሆን ሲኖርበት፤ በእነዚህ ሰዎች ህይወትና ድርጊት ውስጥ የምንመለከተው ግን ሙሉ ለሙሉ ተቃራኒ የሆነ በጎ የሆነውን ነገር የመናቅ ባህርይ ስለሆነ እግዚአብሄርን እናውቃለን ማለታቸው የአንደበት ብቻ መሆኑን ይጠቁመናል።
6. እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሄር ቤትና ለመቅደሱ የሚሆን ነገር ላይ እንኳን ማዋል ባይፈልጉ ብዙ ነገሮችን ለራሳቸው ማድረግ ሲችሉ፤ እነርሱ ግን ብራቸውንና ወርቃቸውን ለራሳቸው ጥፋት በሚሆነው ጣዖትን በመስራት ላይ እንዳዋሉት ነው የምናነበው። ከእግዚአብሄር ጋራ ምንም ዓይነት ምክር ሳይጠይቁና ፈቃዱን ሳያውቁ በራሳቸው የወሰዷቸው ሁለቱ እርምጃዎች፤ የመጀመሪያው ያለ እርሱ ፈቃድ ነገሥታትን ማንገሳቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ እርሱን ሳይጠይቁ አለቆችን መምረጥ ናቸው።
7. እነዚህ ሰዎች ነፋስን ዘርተው የሚያጭዱት አውሎ ነፋስን ሆኖባቸዋል፣ የሚዘሩት ዘር አገዳው ዛላ የሌለውና ዱቄት የማይገኝበት ሆኗል፣ እህል አፍርቶ ቢገኝ እንኳን እነርሱ ከመብላታቸው በፊት ባዕዳን ይበሉታል፣ እስራኤል በአህዛብ መሃል ተውጠው ዋጋ እንደሌለው ዕቃ ሆነዋል። ኤፍሬም ለሃጥያቱ ማስተሰረያ የሚሆን ብዙ መሰዊያዎችን እንደሚሰራ ቁ11 ይነግረና፤ ነገር ግን የኤፍሬም ጥፋቱ ለመልካም ብሎ የሚጀምራቸው ነገሮችን እንኳን ወደ ክፉ ቀይሮ የሃጥያት መሰዊያ አድርጎ እንደሚጠቀምባቸው ነው የምናነበው።
8. በቁ12 ላይ እግዚአብሄር በኤፍሬም ላይ ደስ እንዳልተሰኘ የሚናገርበት ነገር፤ እግዚአብሄር ህጉን ራሱ እንደጻፈውና እንደመመሪያ እንደሰጣቸው፤ እነርሱ ግን ሕጉን ልክ እንደ እንግዳና ባእድ ነገር እንደቆጠሩት ነው ጌታ የሚናገረው።

# ጥናት ስድስት ሆሴዕ 9፡1-10፡15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በአካባቢዋ እንደሚገኙት ህዝቦች እስራኤል ደስታና ሃሴት እንዳታደርግ እግዚአብሄር የከለከላት ምክንያት፤ ቁ1 ላይ እንደምንመለከተው እስራኤል ለአምላኳ ታማኝ ስላልሆነችና ለጋለሞታ የሚከፈለውን ዋጋ ወይም ደግሞ የሃጥያትን ዋጋ ስለወደደች ነው። ከነዚህ ከሁለት ጥቅሶች መማር የምንችለው ነገር፤ ደስታና ሃሴት የሚገኘው በጌታ ውስጥ እንደሆነ፤ ሆኖም የእግዚአብሄርን ነገር ናቅ አድርገን የሃጥያትን ዋጋ መከተል ከመረጥን እግዚአብሄር የሚሰጠውን ደስታና ሃሴት ከእኛ ሊወስድ እንደሚችል፤ ወይም ደግሞ ሃጥያት የውስጥ ደስታችንን ሊሰርቅ እንደሚችል እንማራለን።
2. ይህ ቁጥር 8 ላይ የምንመለከተው እውነት፤ ነብያቱ ለኤፍሬም ከእግዚአብሄር ጋራ ሆነው ኤፍሬምን እንዳይጠፋ ከክፉ የሚጠብቁ አገልጋዮቹ እንደሆኑ ሲናገር፤ የእግዚአብሄር ህዝብ ግን ለአገልጋዮቹ ያሳይ የነበረው ነገር፤ ነብያቱ በሚሄዱበት መንገድ ሁሉ እየተከታተሉ ማሰናከያ የሚሆንባቸውን ወጥመድ እንደሚያኖሩባቸው፤ በተለይም ደግሞ ከሁሉ ነገር የሚያሳዝነው፤ ወደ አምላካቸውም ቤት ሲገቡ ሁኔታው ሳይቀየር ማለትም በቤተ መቅደስ ውስጥም ጠላትነትን ወይም ጥላቻን እንደሚያሳዩአቸው ቁ8 በግልጽ ያሳየናል።
3. እግዚአብሄር ስለቀድሞ ግንኙነታቸው ሲናገር፤ እስራኤልን ማግኘቱ ለእርሱ የወይንን ፍሬ በምድረበዳ የማግኘት ያህል እንደነበረና፤ አባቶቻቸውንም ማየቱ፣ የመጀመሪያውን የበለስ ፍሬ የማየት ያህል እንደነበረ ነው በሃዘን ትዝታውን የሚናገረው። ወደ ብዔልፌጎር በመጡ ጊዜ በእግዚአብሄርና በእስራኤል መሃል የነበረው መልካም ግንኙነት እንደደፈረሰ የምናነብ ሲሆን፤ ለግንኙነታቸው መበላሸት ምክንያት ሆኖ የተነገረው ነገር፤ ራሳቸውን ለአህዛብ ጣዖት አሳልፈው እንደሰጡ፤ በተጨማሪም ደግሞ በተለይ ዘኍ 25 የዘሙትንም ሃጥያት በማጉላት እግዚአብሄርን እንዳሳዘኑ ይታያል።
4. እግዚአብሄር እስራኤልን የተንዠረገገ ወይን እስኪመስል ድረስ አለምልሞት እንደ ነበረ ሲናገር፤ ከዚህም ጋራ ብዙ ፍሬን እንዲያፈራ አድርጎት እንደነበረ፤ እርሱ ግን ፍሬው በበዛ መጠን ብዙ መሰዊያዎችን እንደሰራ፤ ሌላው ደግሞ፤ እግዚአብሄር በተጨማሪም የእስራኤልን ምድር በብልጽግና ባርኮት ሳለ፤ እነርሱ ግን የጣዖታት ማምለኪያ ዓጸዶችን ለማስጌጫ ተጠቀሙበት። ይህ የእስራኤላውያን አነጋገር በእኔ አመለካከት ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ እንደሆነ እስማማበታለሁ፤ ምክንያቱም እግዚአብሄርን የማክበር ነገር ቅድሚያ ካልተሰጠው የንጉሥ መኖር ብቻውን ምንም ዓይነት ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል ግልጽ ነውና ነው።
5. እስራኤል በጊብዓ ያንን አስከፊ ሃጥያት ማድረግ እንደጀመሩ ብቻ ሳይሆን፤ እግዚአብሄር በቁ9 ላይ ሕዝቡን የሚከሰው አንድ ጊዜ ሃጥያትን ማድረጋቸውና እርሱን ማሳዘናቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ሃጥያት ማድረጋቸውን ያቆሙበት ጊዜ እንዳልነበረና በሃጥያታቸው እንደቀጠሉበት ነው የሚናገረው። በዚህ ሥፍራ ላይ በፈለገ ጊዜ እንደሚቀጣቸው እግዚአብሄር መናገሩ፤ እነዚህ ሰዎች ከቅጣት አምልጠዋል ወይም አይቀጡም ማለት ሳይሆን፤ ቅጣቱ መቼ እንደሚፈጸም የሚወስነው እነርሱ ወይም ደግሞ ማንኛውም ሰው ሳይሆን እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ ለማስገንዘብ የተነገረ ነው።
6. እግዚአብሄር ኤፍሬም እንዲያደርግ የሚመክረውን ሃሳቦች ከቁ12 ላይ ማየት እንችላለን፤ እነዚህም ለራሳቸው ዘርን በጽድቅ እንዲዘሩ፣ ሁለተኛው ደግሞ የጽኑ ፍቅርን ፍሬ እንዲያጭዱ፣ ሶስተኛው ምክር እዳሪውን መሬት እንዲያርሱ ነው፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄርን የሚፈልጉበት ጊዜ እንዲሆንላቸው ነው። እነርሱ ግን ያደረጉት፤ በጽድቅ ፈንታ ክፋትን መዝራት፤ በፍቅር ፈንታ ሃጥያትን ማጨድ፤ አርሰው ከመብላት ይልቅ የሃሰትን ፍሬ እንደበሉ፤ እግዚአብሄርን ከመፈለግም ይልቅ በሰራዊታቸው ጉልበት መታመንን በመምረጥ፤ እግዚአብሄር እንዲያደርጉ የመከራቸውን ነገሮች ሁሉ ተቃራኒ የሆኑትን ነገሮች መርጠው እንዳደረጉ ነው የምንመለከተው።
7. ነብዩን እንደሞኝ፤ መንፈሳዊውን ሰውም እንደ እብድ የቆጠሩበትን ምክንያት ሆሴ 9:7 ሲጀምር ተናግሯል፤ ይኸውም ከሃጥያታቸው መብዛት የተነሳና፤ እስራኤል ከእግዚአብሄር ጋራ የነበረው ግንኙነት የአባትና የልጅ ወይም የወላጅ ግንኙነት መሆኑ ቀርቶ በጠላትነት ህይወት ውስጥ መሆናቸው እንደሆነ ከቁጥሩ ማየት ይቻላል።

# ጥናት ሰባት ሆሴዕ 11፡1-12፡14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ1ላ ከምናነበው የምንረዳው በእግዚአብሄርና በእስራኤል መሃል ያለው ግንኙነት የጀመረው ገና እስራኤል ሕጻን ልጅ እያለና በግብጽ ምድር እያለ እንደሆነ ክፍሉ ይነግረናል። ማቴዎስ ይህንን ስለ እስራኤል የተነገረውን ሃሳብ በነብዩ እንደተነገረው በማለት ሄሮድስ ሕጻናቱን ሁሉ በፈጀ ጊዜ ዮሴፍ በእግዚአብሄር ትዕዛዝ ልጁን ኢየሱስን ወደ ግብጽ ከወሰደ በኋላ ሁኔታው ሲቀየር ተመልሶ እንዲሄ በእግዚአብሄር የተነገረውን ሃሳብ ለመግለጽ ነው ማቴዎስ የተጠቀመበት።
2. እስራኤልን በብዙ ይጣራ እንደነበረ፤ ነገር ግን እነርሱ ደግሞ በዚያው መጠን ይሸሹት እንደነበረ፣ ከዚህም አልፈው ለበዓል አማልክት መስዋዕትን እንደሰውና፣ ለተለያዩ ምስሎችም ደግሞ እንዳጠኑ እንመለከታለን፤ ኤፍሬም መራመድ በማይችልበት በሕጻንነቱ ወቅት ኤፍሬምን እጁን ይዞ መራመድን እንዳስተማረው፣ እነርሱ ግን እንዳላስተዋሉ፤ በርህራሄ ገመድና፣ በፍቅር ሰንሰለት እንደሳባቸው፣ ቀንበርን ከላያቸው ላይ እንዳነሳላቸው፣ ዝቅ ብሎም ምግባቸውን እንደመገባቸው እናነባለን።
3. እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋራ የጀመረውን የፍቅር ግንኙነት እስራኤል ለመኮትኮትና እንዳይበላሽ ለመጠንቀቅ እንቢተኛ መሆኑ ያስከፈለው ነገሮች፡ ወደ ግብጽ እንዲመለሱ፣ አሦር እንዲገዛቸው ተደርገዋል፤ በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ እንዲመዘዝ ሆኗል፣ የበሮቻቸውን መወርወሪያ ይቆርጣል፣ ስለ ክፉ እቅዳቸው እግዚአብሄር ይደመስሳል፣ ወደ እርሱ ቢጣሩም ሰምቶ መልሶ አያከብራቸውም።
4. ከቁ8 በላይ ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በሃጥያት ላይ የሚቆጣ ጻድቅ አምላክ እንደሆነ የሚያስገነዝቡን ሲሆን፤ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር የሚርና የሚራራ፣ ይቅር ባይ አምላክ እንደሆነ እንረዳለን። ከቁጣው ወጥቶ እግዚአብሄር ለህዝቡ እንደሚያደርግላቸው በቁ10-11 ላይ ቃል ሲገባ የምናያቸው ነገሮች፤ እግዚአብሄርን አንፈልግም ያሉት ሰዎች፣ እግዚአብሄርን እንዲከተሉ፤ እንደ ወፍ ከግብጽና፣ እንደ እርግብ ደግሞ ከአሶር እንደሚመጡ፤ ተመልሰውም በኤርሚያስ መጽሐፍ እንደተነገረው በቤታቸው ውስጥ እንደሚያኖራቸው ይናገራል።
5. ቀደም ባሉት ዓመታት ውስጥ እግዚአብሄር እስራኤል ይሁዳን ራሷ በገባችበት የሃጥያት ወጥመድ ውስጥ እንዳታስገባት እያለ ለእስራኤል በሆሴ 4፡15 ላይ የተናገረው ማስጠንቀቂያ፤ ዓመታት ካለፉ በኋላ በሆሴ 11፡12 ላይ የምንመለከተው እንደተፈራው ይሁዳ ለአምላክ የማይገዛና፣ እንዲያውም ከዚያ አልፎ ቅዱሱን የሚቃወም ሆኖ እንደተነሳ እናነባለን። በአንደኛ ደረጃ ኤፍሬም በሐሰት የተሞላ ነው፣ ሁለተኛ ቀኑን ሙሉ የምስራቅን ነፋስ የሚከተል የነፋስ እረኛ ነው፣ ሐሰትንና ዓመጽን ያበዛል፣ ከአሶር ጋር ቃል ኪዳንን ያደርጋል፣ የሚሉትና በመጨረሻም ደግሞ የወይራ ዘይትን ወደ ግብጽ እንደሚልክ ነው የሚከሰው።
6. ቁ2 ላይ የምናነበውና ስለ እግዚአብሄር ፍርድ የሚያስተምረን እውነት ቢኖር፤ እግዚአብሄር ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራውና እንደ መንገዱ እንጂ ሁሉንም ሰው የጅምላ የሆነ ዓይነት ፍርድ እንደማይፈርድ ነው የምንማረው። በመጀመሪያ ደረጃ ያዕቆብ የታገለው ገና ከእናቱ ሆድ ለመውጣት በሚጀምርበት ወቅት ሲሆን፤ ትግሉንም ያካሄደው የወንድሙን የኤሳውን ተረከዝ በመያዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው ትግል ደግሞ ከአምላክ ጋራ በቤቴል በረከትን ለመቀበል ያደረገው ትግል ነው።
7. በቁ6 ላይ የምንመለከታቸው እግዚአብሄር ከሕዝቡ የሚጠብቃቸው ነገሮች በአንደኛ ደረጃ የተጠቀሰው ሕዝቡ ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ፍቅርንና ፍትህን እንዲጠብቁ ሲሆን፤ በሶስተኛ ደረጃ የተነገራቸው ነገር ደግሞ ዘወትር በአምላካቸው እንዲታመኑ የሚሉ ናቸው። እነርሱ ግን በተቃራኒው ሲያደርጉ የሚገኙት፤ ነጋዴው ሐሰተኛ ሚዛን በመጠቀም ነው የሚሸጠው፣ ነጋዴው ማጭበርበርን በመውደድ ሥራዬ ብሎ ይዞታል፣ ኤፍሬም ደግሞ ባለጠጋና ሐብታም ነኝ፣ ሃጥያት የሚባል ነገርም በእኔ ውስጥ አይገኝም በማለት ራሱን በማሳት ላይ ነው የሚገኘው።
8. ይህ ህዝብ ከዚህ ዓይነት መከራ ውስጥ እንዲገባና እግዚአብሄርም ደግሞ እንዲጨክን ሊያደርጉት የሚችሉ ብዙ የተለያዩ ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ብረዳም እንኳን፤ ከሁሉ በላይ ግን ዋነኛውና አሁን ለደረሱበት ደረጃ ያደረሳቸው የሚመስለኝ ነገር ቢኖር በቁ5 መጀመሪያ ላይ የተነገረው "…ንስሃ መግባት እንቢ በማለታቸው" የሚለው ሃሳብ እንደሆነ ነው ይማምነው።

## ጥናት ስምንት ሆሴዕ 13፡1-14፡9 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኤፍሬም ቀድሞ የነበረበትን ሁኔታ ሲናገር፤ ኤፍሬም ሲናገር ሰዎች ይንቀጠቀጡ እንደነበረና፣ እርሱም በእስራኤላውያን ዘንድ የተከበረ እንደነበረ ቁ1 ይናገራል። ኤፍሬም ዛሬ ያለበትን ሁኔታ ደግሞ የሚነግረን ቁ2 ሲሆን፤ እርሱ ሃጥያት መስራትን እንዳበዛ፣ ብሩን አቅልጦ ለራሱ ጣዖት እንደሰራ፣ በጥበብ የተሰሩ ምስሎችን እንዳዘጋጀ፣ ስለነዚህ ዓይነት ሰዎች የተነገረው፤ ሰውን መስዋዕት አድርገው እንደሚያቀርቡና፤ የጥጃ ጣዖቶችንም እንደሚስሙ ነው። ስለዚህም ምክንያት የኤፍሬም ለወደፊት የተዘጋጀለት ነገር፤ እንደ ማለዳ ጉምና ፈጥኖ እንደሚጠፋ የጠዋት ጤዛ፤ ከአውድማ እንደሚጠረግ እብቅ፣ በመስኮትም እንደሚወጣ ጢስ እንደሚሆኑ ነው እግዚአብሄር የሚናገረው።
2. በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሄር ለህዝቡ እንዳደረገለት የሚናገረው ነገር ከግብጽ ምድር የማውጣቱን ነገር ነው፤ በሁለተኛ ደረጃ አደረኩልህ በማለት የሚናገረው ነገር ደግሞ በምድረበዳ፣ እንዲሁም በሃሩር ምድር እንደተንከባከበው ነው። እግዚአብሄር ላደረገላቸው ነገር ደግሞ የሕዝቡ ምላሽ አድርጎ በተዋረድ ያስቀመጣቸው ሶስት ነገሮች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤ ካበላቸው በኋላ እንደጠገቡ፣ በጠገቡ ጊዜ ደግሞ እንደታበዩ፤ በመጨረሻ ደግሞ የእነዚህ ሁሉ ውጤት የሆነው እግዚአብሄርን መርሳት እንዳመጡ እናያለን።
3. ለእስራኤል ለጥፋቱ ምክንያት አድርጎ እግዚአብሄር በቁ9 ላይ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛው እስራኤል በእግዚአብሄር ላይ ስለተነሳ የሚያጠፋው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ረዳቱን እግዚአብሄርን ስለተቃወመ መጥፊያው ይሆናል ማለት ነው። በቁ10 እና 11 ላይ ንጉስ በማለት እግዚአብሄር የሚናገርለት ሰው ሳዖል እንደሆነ ነው የማምነው፤ ይህንንም ለማለት ያስቻለኝ ምክንያት በቁ11 ላይ "ንጉስ ስጠኝ" የሚለው አነጋገር፣ በቁ11 ላይ ደግሞ "በቁጣዬ ንጉስ ሰጠሁህ" እና "በመዓቴም ሻርኩት" የሚሉት አነጋገሮች ሁሉ ለሳዖል በትክክል የሚሰሩ ስለሆነ ነው።
4. ሕጻን ልጅ ከእናቱ ማህጸን ውስጥ አዲስ ህይወትና አዲስ ጅማሬን ይዞ እንደሚወጣ ሁሉ፤ ምንም እንኳን የኤፍሬም ሃጥያት ጽዋው ሞልቶና የእግዚአብሄርን መዝገብ ሞልቶት ቢገኝም እንኳን፤ እግዚአብሄር አምላክ ለኤፍሬም እንደ አዲስ ህጻን አዲስን ህይወት እንዲጀምር እድል እንደሰጠው ከቁ13 ላይ እናነባለን። ኤፍሬም ከዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሄርን ቸርነት ማየት እንዳቃተው፤ ስለዚህም እግዚአብሄር "እርሱ ግን ጥበብ የሌለው ልጅ ነው" በማለት በቁ13 ላይ ምላሹን ሲነቅፍ እናገኘዋለን።
5. በነብዩ ሆሴዕ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሄር በሆሴ 14፡1-2 ውስጥ የሚናገረውን ሃሳብ በአንድ ቃል ብቻ ግለጽ ብባል፤ "ተመለሱ" የሚለው ቃል አጠቃላይ ሃሳቡን ይገልጻል የሚል እምነት አለኝ። እስራኤል ወደ እግዚአብሄር ለንስሃ ሲመጣ፤ "ሃጥያታችንን ሁሉ ይቅር በለን"፣ "የከንፈራችንን ፍሬ እንድናቀርብ በምህረትህ ተቀበለን"፣ "አሶር ሊያድነን አይችልም"፣ "በጦር ፈረሶችም ላይ አንቀመጥም"፣ "ከእንግዲህ የገዛ እጆቻችን የሰሯቸውን አምላኮቻችን አንላቸውም" የሚሉት በንስሃቸው ውስጥ መካተት እንዳለባቸው ይመክራቸዋል።
6. ከዳተኛነታቸውን ይፈውሳል፣ እንዲሁ ይወዳቸዋል፣ እሱ ለእስራኤል እንደ ጠል ይሆናቸዋል፣ እስራኤል እንደውብ አበባ ያብባል፣ እንደ ሊባኖስ ዝግባ ሥር ይሰዳል፣ ቅርንጫፉ ያድጋል፣ ውበቱ እንደ ወይራ ዛፍ፤ ሽታውም እንደ ሊባኖስ ዝግባ ይሆናል፣ ሰዎች እንደገና ከጥላው ሥር ያርፋሉ፣ እርሱ እንደ እህል ይለመልማል፣ እንደ ወይን ተክል ያብባል፣ ዝናውም እንደ ሊባኖስ የወይን ጠጅ ይወጣል። እግዚአብሄር በዚህ ሥፍራ "እንዲሁ እወዳቸዋለሁ" ማለቱ እኔ እንደምረዳው ከሆነ፤ ፍቅሩ እነርሱ በሚያደርጉት ነገር ላይ የተመሰረተ እንደማይሆንና ስለማንነቱ ብቻ የሚያደርገው ነገር እንደሆነ ሲሆን፤ ይህ ማለት ግን ሲያጠፉ አይቀጡም ማለት እንዳልሆነና አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚቀጣም መዘንጋት የለብንም።
7. እስራኤል እግዚአብሄር በነገረው ጎዳና ከሄደ፤ በእግዚአብሄርና በእስራኤል ግንኙነት ላይ የሚታይውን ለውጥ የሚናገሩት ሃሳቦች በቁ8 ላይ የማያቸው ሃሳቦች፡- አንደኛው ኤፍሬም ከእንግዲህ ወዲህ ከጣዖት ጋራ ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖረውም፣ የሚሰማውና የሚጠነቀቅለት ጣዖቱ ሳይሆን እግዚአብሄር ይሆናል፣ ለኤፍሬም እንደለመለመ የጥድ ዛፍ ይሆንለታል፣ ከእግዚአብሄር የተነሳም ፍሬአማ ይሆናል።
8. በዚህ ቁጥር ላይ ጥበበኛ ሰው እንደሚያስተውለውና፤ አስተዋይ የሆነ ሰው እንደሚረዳው የተነገረው ነገር፤ የእግዚአብሄር መንገድ እውነትና ቀና እንደሆነ መረዳትና ማስተዋል ነው።